# በሰሜን ኣሜሪካ ዋሺንግተን ዲስ ከተማ የኖርዌይ ኤምባሲ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ ተካሄደ

አጭር ዘገባ




በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግተን ዲሰና አካባቢው በሚገኙ ኢትዮጵያውያን በኖርዌይ ነዋሪ በሆኑ የኢትዮጵያ ስደተኞች ላይ የተወሰነውን በግድ ወደ ሀገር የመመለስ ውሳኔ በመቃወም በአጭር ጊዜ የሰላማዊ ሰልፍ ማስታወቂያ ጥሪ አጥጋቢ የሆነ የወገን አድን ሰላማዊ ሰልፍ በኖርዌይ ኤምባሲ ፊት ለፊት ማርች 14 ተካሂዷል።



ይህ ሰላማዊ ስልፍ ከላይ እንደተገለጸው በወያኔ መሰሪ ሴራ አማካኝነት በኖርዌይ የሚገኙ በመቶዎች በሚቆጠሩ ስደተኛ ወገኖቻችንን አስገድዶ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የኖርዌይ መንግሥት እያካሄደ ያለውን ኢሰብዓዊ ድርጊት በመቃወም ነበር።




ሰልፉ ባለፈው ሳምንት የተጀመረውና በየሃገሩ እየተካሄደ ያለውን እንቅስቃሴ ድጋፍ የሚሆን ሲሆን ምንም እንኳን የሥራ ቀን ቢሆንም በሰልፉ ላይ ብዛት ያላቸው ሃገር ወዳዶች ተገኝተዋል። በዚህ ሰልፍ ላይ የኢሕአፓ ፣ የኢወክንድ ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያዊነት ራዲዮ አዘጋጅና ከሌሎች ሃገር ወዳዶች ጋር በመሆን ተገኝተው ድምቀትን ሰጥተውታል ።




ከዚህም በማያያዝ ካለፈው ዕሁድ ጀምሮ በኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት አባላት በኢትዮጵያውያን ንግድ ማዕከልና ቤተ ኃይማኖት በመዘዋወር ለመላው

ስደተኞች መብትን የሚጠይቅ የፊርማ ማሰባሰብ ተደርጎ በሺህ የሚቆጠሩ ፊርማዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል።




በዚሁ ሰላማዊ ሰልፍ ወቅት የኤምባሲው ሃላፊዎች ከሰላማዊ ሰልፈኞቹ ተወካዮች የተጻፉ ደብዳቤዎችን ተቀብለዋል።



በመጨረሻም ተከታታይ እንቅስቃሴ እንደሚደረግ የሰልፉ አዘጋጆች ገልጸው ሰላማዊ ሰልፉ ተጠናቋል።